# አጓጉል ጥያቄ የተሳሳተ መልስን ያስገኛል

የሕዝብ ትግልን ከግብ ለማድረስ የተነሱ ድርጅቶች ከሁሉም በፊት የሀገራቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ማወቅ መቻል አለባቸው:: ማነው ጠላት ማነው ወዳጅ ከሚለው የሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ባሻገር በጎረቤትና ዓለም አቀፍ ደረጃም መመርመር ያለበት ነው:: ይህ ምላሽ ካገኘ ምን ማድረግ አለብን ለመሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ መስጠት ይቻላል::

ጥያቄው አራምባ ከሆነ መልሱ ቆቦ መሆኑ የማይቀር ነው:: ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ሁኔታ ይፈጠራል:: ለዚህም ነው ምንድነው ችግሩ፣ ምንድነው ዋናው ጥያቄ የሚለውን በስርዓት መያዝ የሚያስፈልገው:: ጥያቄው ከተዛባ መልሱም ይምታታል:: ለዓመታት ሰላማዊ ትግል ወይስ ትጥቅ ትግል ብለው ሁለቱን ስልቶች ነጣጥለወና አቃርነው ያነታረኩን ክፍሎች ያደረሱት ጉዳትና ለወያኔም የጠቀሙት የሚዘነጋ አይደለም:: ዱላና ብረት ተፈላጊ ው መላ ሆኖ ባለበት ዱላ ወይስ መላ በሚል የተጀመረውን የትጥቅ ትግል አንቅስቃሴ ያጠቁ ትንም የምንረሳቸው አይደሉም:: በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሀገሬ ወይስ ድርጅቴ በሚል የሚሰነ ዘር ትችት አለ :: ብዙ ጊዜና በተለይም ኢሕአፓን ያጠቁ የሚመስላቸው ክፍሎች ኢሕአፓ ዎች ድርጅታቸውን ከሀገራቸው አስበልጠው ይወዳሉ ብለው ለመክሰስ ይጥራሉ :: የጥያቄ ው አቀማመጥ ራሱ በጣም የተሳሳተ ነው:: ድርጅቴና ሀገሬ የተያያዙ ናቸው:: አንዱ ከአን ዱ ከተነጠለ ስህተት ይፈፀማል:: ኢሕአፓዎች ለምሳሌ ድርጅታቸውን የሚወዱት ይህ ድርጅት ለሀገራቸው ለመታገል ዓይነታ መሳሪያቸው በመሆኑ ብቻ ነው:: ሀገራቸውን ባይወ ዱ ድርጅታቸውን አይወዱም ብቻ ሳይሆን አይፈልጉትም:: አንዳንዶች ከጥቂት ዓመታት በፊት ኢሕአፓ እውን ሀገሩን ከወደደ ራሱን አፍርሶ በሌላ ድርጅት ስር ይታገል ብለው ሲመክሩ ነበር:: ይህንን ምክር ኢሕአፓ ያልተቀበለው ከሀገሩ ድርጅቱ በልጦበት ሳይሆን ሀገሩን በማስቀደሙና የተመከረው እርምጃ ፍፁም ጠቃሚ አለመሆኑን በመገንዘቡ ነው:: ሌላ ድርጅት የተባለውም ለሀገር ከመታገል አንፃር አመርቂ ውጤትን የሚያስገኝ ባለመሆኑ (ኢሕአፓ ይህን ከጠዋቱ በማወቁ) የትግል መሳሪያ የሆነውን ኢሕአፓን ማፍረስን ጠቃሚ ብሎ አልተቀበለውም:: ለዚህም ነው ድርጅት ወይስ ሀገር ብለው አጓጉል ጥያቄ የሚያቀርቡ የፖለቲካን ሀሁ ገና ያልተረዱ ያልጨበጡ ሆነው የሚገኙት::

ኢሕአፓ ለሀገር ብሎ ከወጉት፣ ካደሙትና ከጎዱት ድርጅቶች ጋር ሳይቀር በህብረት ተያይ ዞ ሲታገል ቆይቷል:: እነዚህ የህብረት ጥረቶች ሊያደርጉ የሚችሉትን አስተዋፅዖ አድርገው አልፈዋል:: ያበቁበት ምክንያት ደግሞ ለማንም ግልፅ ነው:: ኢሕአፓን በውህደት ሂደት ሊከቱት የሞከሩ ቡድኖችን በተመለከተ ይህ ሂደት ለትግሉም ሆነ ለሀገርም ቅንጣት ጥቅም የማይሰጥ በመሆኑ ኢሕአፓ አልዋሀድም ብሏል::ይህ ውህደት ህልውና ይሰጠናል፣ ይጠቅመ

ናል ያሉት ግን ይህን የኢሕአፓ እምቢታ በድርጅት መውድድና ሀገርን መጥላት ሊመዘግቡ ና ድርጅቱን ሊያስወቅሱ ሲጥሩ ጊዜን አጥፍተዋል። ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ነው። የወያኔ ዋና ጠላትና የሕዝብም መሳሪያ የሆነውን ኢሕአፓን መውደድ ሀገርን መውደድ ነው። ድርጅቱ ም ሀገሬም ነው መፈክሩ። በዚህ መሀል ግንብ ሊያቆሙ የሚሹት ለሀገር አይጠቅሙም። ስለዚህም የተሳሳቱ ጥያቄዎችን መደርሩንና ውዠንብርን መፍጠሩን ብንተው የተሻለ ይሆና ል።